*ጋዜጣዊ መግለጫ*

አይቬኮ እና አምቼ 15 ዴይሊ ተሽከርካሪዎች ለኢስት አፍሪካ ቦትሊንግ አክሲዮን ማህበር የኮካ-ኮላ ለስላሳ መጠጦች አምራች እና አከፋፋይ በኢትዮጵያ አስረከቡ

- ለሁለገብነት ዝናው ታማኝ የሆነው አይቬኮ ቀላል የንግድ ተሽከርካሪ በከተማ ውስጥ ዕቃዎችን ከማከፋፈል እስከ ከባድ ጭነት ትራንስፖርት ድረስ መጠነ ሰፊ የተለያዩ ተልእኮዎችን ይፈጽማል፡፡
- ከምቼ ስፖንጅ የተሰሩት የሹፌር መቀመጫ፣ የጀርባ እና የጭንቅላት መደገፊያ ለአሽከርካሪው ተጨማሪ ምቾትን ይሰጣሉ፡፡

አዲስ አበባ፣ ታህሳስ 05፣ 2016 ዓ.ም

አይቬኮ እና በኢትዮጵያ የንግድ ወኪሉ የሆነው አምቼ ለመጀመሪያ ጊዜ ለማንኛውም ተልእኮ ፍጹም ምቹ የሆኑ በቁጥር 15 ዴይሊ የቀላል ጭነት ተሽከርካሪዎችን ለረዥም ጊዜ ደንበኛቸው ለሆነው ኢስት አፍሪካ ቦትሊንግ አክሲዮን ማህበር (EABSC) ብቸኛ የኮካ-ኮላ ምርቶች አምራች እና አከፋፋይ በኢትዮጵያ አስረከቡ፡፡ አምቼ እስከ አሁን ድረስ ላለፉት 16 ዓመታት ከኮካ ኮላ የለስላሳ መጠጦች አፍሪካ የንግድ አጋሮች ውስጥ አንዱ ሲሆን በዓለም ታዋቂ ለሆነው ለዚህ የለስላሳ መጠጦች አምራች ኩባንያ በየዓመቱ አይቬኮ የከባድ ፣የመካከለኛና ቀላል ጭነት ተሽከርካሪዎችን ሲሸጥ የነበረና በጥቅሉ በቁጥር ከ200 በላይ የአይቬኮ የጭነት ተሽከርካሪዎችን አቅርበዋል፡፡

በአምቼ በታህሳስ 05 ቀን በተካሄደው ሥነ ሥርዓት ላይ የተረከቡት ሁሉም የአይቬኮ ምርት የሆኑት Daily70C15/E3፣ ባለ ሁለት አክስል ተሽከርካሪዎች ናቸው፡፡ እነዚህ በአምቼ መኪና መገጣጠምያ የተገጠሙት ተሽከርካሪዎች ኮካ-ኮላ ኩባንያ ምርት ማከፋፈል ስራ ላይ ከተሰማሩት ሌሎች ተሽከርካሪዎች ጋር አብሮ ይሰማራሉ፡፡

በተሽከርካሪዎቹ ርክክብ ላይ የተገኙት የአምቼ ዋና ሥራ አስኪያጅ የሆኑት አንቶኒዮ ካሩሶ፡ “በዚህ ስኬት እጅግ ተደስቻለሁ፡፡ ይህ ኢስት አፍሪካ ቦትሊንግ አክሲዮን ማህበር ጋር የተደረገው ርክክብ አይቬኮ በኢትዮጵያ ውስጥ በደንበኞቻችን ዘንድ የመጀመሪያ ምርጫ መሆኑን የሚያሳይ ከመሆኑም ባለፈ በተስማሚ የስራ ሁኔታ የአይቬኮ ዴይሊ የላቀ የማሽርከር ተሞክሯችንን ስናቀርብ ደስ እያለን ነው፡፡” በማለት ተናግረዋል፡፡

የአምቼ የሽያጭ ክፍል ተወካይ የሆኑት አቶ መኮንን ተስፋዬ፡ “ኢስት አፍሪካ ቦትሊንግ አክሲዮን ማህበር ጋር የተካሄደው የንግድ ስምምነት አካል በመሆኔ ደስተኛ ከመሆኔም ባለፈ በሂደቱ ወቅት በሁለቱም ኩባንያዎች የስራ ሀላፊዎች ለተደረገልኝ ድጋፍ በእጅጉ አመሰግናለሁ፡፡’’ በማለት አክለዋል፡፡

አይቬኮ ዴይሊ:የህልምዎን መኪና ያሽከርክሩ

ዴይሊ በአይነቱ ሁለ ገብ ተሽከርካሪ ነው፡፡ የተሽከርካሪው የላቀ አገጣጠምና የአካል ስራ አማራጮቹ መጠነ ሰፊ እድሎችን የሚፈጥሩ ሲሆን ተልእኮዎ ምንም ይሁን ምን ዴይሊን ለንግድ ስራዎት መስፈርቶችዎ ፍጹም ተስማሚ ሆኖ ያገኙታል፡፡

ዴይሊ ለገበያው የተለያዩ አማራጮች ያቀርባል - ተሽከርካሪው ከ3.5 እስከ 7.2 ቶን ጠቅላላ ክብደት የሚጭን፣ ከ3000 እስከ 5100 ሚሜ የጎማ ርቀት ያለው ተሽከርካሪ በማቅረብ በአይነቱ የመጀመሪያ ሲሆን ይህም በከተማ ውስጥ ዕቃዎችን ከማከፋፈል እስከ ግንባታው

ዘርፍ የከባድ ጭነት ትራንስፖርት ስራዎች ድረስ ለተለያዩ አይነት ተልእኮዎች መጠነ ሰፊ እድሎችን ይከፍታል፡፡ ተሽከርካሪው የተዘጋጀው በተለያዩ አይነት የአካል ስራ አማራጮች መሆኑ ለልዩ ልዩ ፍላጎቶዎችን ለሚማላት ቀላል ያደርገዋል፡፡ ተሽከርካሪው እንደ የህይወት አድን ተሽከርካሪ ወይም አምቡላንስ ላሉ ልዩ ሙያዎች ፍጹም ተስማሚ ነው፡፡

አዲስ ምቹ የስፖንጅ ወንበሮች: ለሹፌሩ ከፍተኛ ምቾት እንዲሰጡ ታስበው የተዘጋጁ

ከስፖንጅ የተሰሩ የመቀመጫና የጀርባ መደገፊያ ክፍል ያለው ሙሉ በሙሉ አዲስ የሹፌር ወንበርን የሚይዙት የዴይሊ ስራቶች - የኢንዱስትሪው የመጀመሪያ ቀላል የንግድ ተሽከርካሪዎች ናቸው፡፡ የሰውነት ክብደትን በምቾት እንዲያሳርፍ ተስተካክሎ የተሰራው የስፖንጅ ወንበር የሰውነት ክብደት ጫናን በ30% ይቀንሳል፡፡ ይህም እጅግ ከፍተኛ ምቾት ከመስጠቱም ባለፈ የጀርባ ህመምን ይከላከላል፡፡ የጎን መደገፊያዎቹ ዘና ብሎ መደገፍን፣ ደህንነትን እና የማሽከርከር ተሞክሮን ለማሻሻል 15 ሚሜ ውፍረት ካለው ስፖንጅ የተሰሩ ናቸው፡፡ ለረጃጅም ሰዎች 20 ሚሜ ርዝመትና 15 ሚሜ ውፍረት ያላቸው ባለመደገፊያ የፊት ወንበሮች የተዘጋጁለት መሆኑ እግሮቻቸውን በአግባቡ እንዲያስደግፉ ያስችሏቸዋል፡፡ የጎን መደገፊያዎቹ በቀላሉ ወደ ተሽከርካሪው ለመግባት እና ለመውረድ እንዲያስችሉ ተደርገው መዘጋጀታቸው ተደጋጋሚ መውጣትና መውረድን ለሚጠይቁ የቤት ለቤት የማከፋፈል ስራዎች አቅርቦቶች ተመራጭ ያደርገዋል፡፡

አይቬኮ

አይቬኮ የተለያዩ አይነት የቀላል፣ መካከለኛና ከባድ ጭነት ተሽከርካሪዎች፣ ለፒስታ መንገድ የሚያገለግሉ የጭነት መኪኖች እና ለማንኛውም የአካል አይነት የሚስማሙ ተሽከርካሪዎችን አምርቶ ለገበያ የሚያቀርበው የአይቬኮ ግሩፕ ኤን.ቪ. (EXM: IVG) የንግድ ምልክት ነው፡፡

ድርጅቱ ለእያንዳንዱ ደንበኛ ከተልዕኮው ጋር በትክክል የሚስማሙ ተሽከርካሪዎችን ለማቅረብ በምርት ውጤቶቹ ላይ በቋሚነት ፈጠራዎችን በመፍጠር ያስፋፋል፡፡ የሙሉ አገልግሎት አቅርቦቱ የሚያተኩረው በአሽከርካሪዎች ዙሪያ ሆኖ ደህንነትና ምቾት ላይ ትኩረት በማድረግ ምርጥ ተሞክሮ ለማቅረብ ነው፡፡ ባለንብረቶችን ስምሪታቸውን በአይቬኮ የተሚሉ የትራንስፖርት ውጤቶች እንዲያሻሽሉ ለመርዳት የተለያዩ አይነት የተሻሻሉ የዲጂታል፣ ግንኙነት የተሚላላቸው አገልግሎቶች ይዘጋጃሉ፡፡

አይቬኮ ተጨማሪ የባትሪ ሚቴን፣ የባትሪ ኤሌክትሪክ እና የነዳጅ ሴል ቴክኖሎጂዎችን ማልማትን የሚይዝ የተለያየ የሀይል አቀራረብን በመከተል የካርቦን ልቀትን ለመቀነስ ስትራቴጂ ይተጋል፡፡

አይቬኮ 6 የመኪና ማምረቻዎችን እና 7 የምርምርና ልማት ማእከላትን ስራ ላይ አውሏል፡፡ ድርጅቱ በ160 አገራት ውስጥ 3,500 የሽያጭና አገልግሎት ጣቢያዎች ያሉት ሲሆን የአይቬኮ ተሽከርካሪ በሚሰራበት ቦታ ሁሉ የቴክኒክ ድጋፍ ዋስትና ይሰጣል፡፡

አይቬኮ ለደንበኞቹ እጅግ አስተማማኝ አጋር እና የሙሉ ጊዜ ሚና ተጫዋች የመሆን ህልም አንግቦ የትራንስፖርት ኢንዱስትሪውን ለማሸጋገር በለውጥ መንገድ ላይ ይገኛል፡፡